
# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ




### ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፤


* ቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ ምንነት በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* የተለያዩ የቀይ መስቀል አገልግሎቶችን በኢምቋ ትዘረዝራላችሁ፤
* የቀይ መስቀል/የቀይ ጨረቃ አገልግሎት ለሀገር እድገት ያለው አስተዋጽዖ በኢምቋ ታብራራላችሁ፤
* ከሕክምናና መድኃኒት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ምልክቶችን ትዘረዝራላችሁ፤
* የተለያየ ይዘት ኖሯቸው በተመሳሳይ ምልክት የሚገለጹ ምልክቶችን በተለያዩ ምልክቶች የመግለጽ ክሂሎት ታዳብራላችሁ።

## ቁልፍ ምልክቶች






አልኮል




ጥጥ




ፋሻ




የቁስል ፕላስተር




የዐይን ጠብታ




ፋርማሲስት




መቀስ




ወረንጦ




ጉሉኮስ




ጓንት



የቁስል ቅባት



ነርስ



ፋርማሲ

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መመልከትና መግለጽ

ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን ሥዕልተመልክታችሁ፣ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ።

1. በሥዕሉ ላይ ምን-ምን ነገሮችን ተመለከታችሁ?
2. በሥዕሉ ላይ የምትመለከቷቸው ቁሳቁሶች አገልግሎታቸውምንድን ነው? በኢምቋ ዘርዝሩ።
3. በሥዕሉ ላይ የምትመለከቷቸው ቁሳቁሶች በአብዛኛው የሚገኙት የት ነው?









# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## አንብቦ መረዳት

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በአንቀጽ ተከፋፍላችሁ፣ ካነበባችሁ በኋላ የአንቀጾችን ፍሬ ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ::

### የቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ አገልግሎት

ከቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ አገልግሎት አንዱ ነው:: የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ለማድረግ በቅድሚያ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን መለየት ይገባል:: ለመጀመሪያ ሕክምና የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ቀለል ላሉ ጉዳቶችና ከባድ ጉዳት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ወደ ሐኪም ቤት እስኪወሰዱ ድረስ የደረሰባቸው ጉዳት እንዳይባባስና፣ ለከፋ ጉዳት እንዳያጋልጣቸው የምንጠቀምባቸው የዕርዳታ ዓይነቶች ናቸው:: ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ተዘርዝረው በቀላሉ ለማንቀሳቀስ በሚያስችል ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው::

አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ይወድቃሉ:: በመውደቃቸውም ልዩ ልዩ የአካል ክፍላቸው የመላላጥ ወይም የመሰበር ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል:: ሊፈነከቱ ወይም በእሳት ወይም በፈላ ውኃ ሊቃጠሉ ይችላሉ፤ መርዛማ በሆኑ ነፍሳት ሊነደፉ ወይም በኤሌክትሪክ ሊያዙ የሚችሉበት አጋጣሚም አለ:: ራሳቸውን ስተው ሊወድቁ ይችላሉ፤ ነስር ሊያጋጥማቸው ይችላል:: በአጠቃላይ ተማሪዎች ልዩ ልዩ ከባድና ቀላል ጉዳት ሊደርስባቸው ስለሚችል፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ የቀይ መስቀል ክበብ ወይም የትምህርት ቤቱ ክሊኒክ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን በንጽሕና አዘጋጅቶ ማስቀመጥ ይኖርበታል::

በመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ሳጥን ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው:: ጥጥ፣ለስላሳ ወረቀት (ለቁስል ማጽጃ)፣ አልኮል(ኮፒ)፣ መለጠፊያ ፕላስተር (ትንንሽ ቁስለቶችን መሸፈኛ)፣ የጥጥ ጨርቅ (የቁስል ፋሻ) ረዘም ላለ ጊዜ ቁስልን ሊሸፍን የሚችል፣ የተለያዩ ስፋትና ጥንካሬ ያላቸው ፋሻዎች ( ቁስለቱ በአንድ ቦታ እንዲጸና ለማድረግና ስብራትን ለመጠገን) የሚያገለግል፣ መርፌ ቁልፍ (የተጠቀለለውን ፋሻ ማያያዣ)፣ መቀስ (ለፕላስተርና ለፋሻ መቁረጫ)፣ ባለ ወንጭፍ ሻርፕ (የተጎዳ

ክንድ መደገፊያ)፣ ወረንጦ (ሰውነት በስተው የገቡ ሹል ነገሮችን ማስወገጃ)፣ የዐይን ጠብታ (ዐይን ውስጥ የገቡ ተሕዋስያንና ቆሻሻ ለማስወገድ) የሚያገለግል፣ የአደጋ ጊዜ ቅባት (በእሳት ወይም በፀሐይ ቃጠሎ ለተሰነጣጠቀ ቆዳ ወይም በነፍሳት ለተነደፈ ቆዳ የሚቀቡ)፣የፕላስቲክ ጓንት/ግሎቭ/ (በሕክምና ላይ በደም ንክኪ የሚመጣ በሽታን ለመከላከል)፣የሚወገድ ከረጢት (የተጠቀምንባቸውን የጽዳት ዕቃዎችን ማስወገጃ)፣ ሳሙናና ንጹሕ ውኃ ይጠቀሳሉ።

የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው አደጋዎች የሚባሉት፣ በስለታም ነገሮች መቆረጥ፣ በመውደቅና በመንሸራተት የሰውነት መላላጥና መጋጋጥ፣ የቁስል መድማት፣ የቆዳ መበለዝ ወይም ሰንበር ማውጣት፣ ነስር፣ በምግብ መታነቅ፣ በኤሌክትሪክ መያዝ፣ የአጥንት ስብራትና የአጥንት መሰንጠቅ፣ በዐይን ውስጥ ቆሻሻና ልዩ ልዩ ተሕዋስያን መግባት፣ በመርዛማ ነፍሳት መነደፍ፣ በፈላ ውኃ መቃጠል ወዘተ ናቸው።

ለአነስተኛ መቆረጥና የቆዳ መላላጥ በንጹሕ ውኃና በንጹሕ ጨርቅ በሳሙና በመታጠብ አነስ ባለች ንጹሕና ደረቅ ፎጣ ጫን ጫን እያሉ ቁስሉን በማድረቅ በፋሻ መሸፈን ያስፈልጋል። ያጋጠመው መቆረጥ ከባድ ከሆነ ደሙ እንዳይፈስ የተቆረጠውን ቦታ ከፍ አድርጎ በመያዝ በአፋጣኝ ወደ ሐኪም ቤት መውሰድ ያስፈልጋል።

ሰንበር ወይም የቆዳ መበለዝ የሚፈጠረው በተሰነጠቀ ቆዳ ስር በሚታመቅ ደም ምክንያት በመሆኑ ሰንበር ያለበት ቦታን ጠንከር አድርጎ ጫን ጫን በማድረግ ሰንበሩን ማስወገድ ይቻላል። ሰንበሩ ወይም መበለዙ አስከፊ ከሆነ በበረዶ ወይም በቀዝቃዛ ውኃ በተነከረ ንጹሕ በማሸት መበለዙን ማጥፋት ይቻላል።

ነስር በልጆችና ወጣቶች ዘንድ የተለመደ ነው። ነስር በሚያጋጥምበት ወቅት ግለሰቡን ከጭንቅላቱ ወደፊት ዘንበል ብሎ እንዲቀመጥ በማድረግ ለአሥር ጊዜ ያህል አፍንጫውን ቆንጠጥ ቆንጠጥ (በአውራ ጣትና በአመልካች ጣት አፍንጫውን ይዞ ጫን ጫን) ማድረግ ነው። በዚህ ጊዜ መድማቱ ካልቆመ በአፋጣኝ ወደ ሐኪም ቤት መላክ ያስፈልጋል።

ልጆች በምግብ የመታነቅ አደጋ ሲያጋጥማቸው ከላይ ወደታች በመዘቅዘቅ ከሦስት እስከ አራት ጊዜ ጀርባቸውን መታ መታ ማድረግ ያስፈልጋል። በምግብ የመታነቅ አደጋ ያጋጠማቸው በዕድሜ ከፍ ያሉ ሰዎች ከሆኑ ቀጥ ብለው እንዲቆሙ በማድረግ፣ ወገባቸውን ከደረታችን ጋር አስጠግተን በሁለት እጆቻችን ደረታቸውን ጫን በማድግ በቀላሉ በምግብ የመታነቅ አደጋን መከላከል ይቻላል።

የአጥንት ስብራትና መሰንጠቅ ሲያጋጥም የተሰበረውን ቦታ በራጅ /X-RAY/ በመለየት አስፈላጊውን ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል። ዐይናችን ውስጥ ቆሻሻና ተህዋስያን ሲገቡ በመታጠብና የዐይን ጠብታ በማድረግ ዐይናችን ውስጥ የገባውን ቆሻሻና ተሕዋስያን ማስወገድ ይቻላል።

ልጆች በመርዛማ ነፍሳት ሲነደፉ ለሕመም ማስታገሻ ቅባት በመቀባት ወዲውኑ ሐኪም ቤት መውሰድ ያስፈልጋል። ሳማ ሲለበልባቸውና ንብ ሲነድፋቸው ግን ፀረ-መለብለብ ቅባት መቀባት ብቻ በቂ ነው።

(የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኀበር፣ 2015፣ ካዘጋጀው ጽሑፍ ለዚህ ጽሑፍ እንዲስማማ ተሻሽሎ የተወሰደ።)

## መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት አጫጭር መልስ በጽሑፍ ከመለሳችሁ በኋላ፣ለመምህራችሁ በኢምቋ ግለጹ።

1. ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ።
2. የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ጉዳቶች ምን-ምን ናቸው?
3. የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?
4. ስንበር ወይም የቆዳ መላላጥ የሚያጋጥመው በምን ምክንያት ነው?
5. በፈላ ውኃ መንፈርና በእሳት የመቃጠል አደጋ ሲያጋጥም የሚደረገው የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ምን ዓይነት ነው?
6. ልጆችና በእድሜ ከፍ ያሉ ሰዎች በምግብ የመታነቅ አደጋ ሲያጋጥማቸው የሚደረግ የመጀመሪያ የሕክምና ዕርዳታ ምን-ምን ናቸው?
7. በምንባቡ መሠረት በልጆችና በወጣቶች የተለመደ የጉዳት ዓይነት ምንድን ነው?
8. የራጅ ምርመራ የሚያስፈልገው ለምን ዓይነት ጉዳት ነው?
9. የፀረ-መነደፍ ወይም የፀረ-መነደፍ ቅባት ጠቃሜታ ዘርዝሩ።

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ውይይት

በቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ አገልግሎት ዙሪያ በመምህርና በተማሪዎች መካከል የተደረገ ውይይት።

**መምህር:** ቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ምን-ምን ናቸው?

**አልማዝ:** በጦርነት፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በጎርፍ፣ በረሃብ፣ በተላላፊ በሽታዎች፣ ወዘተ፣ ምክንያት የተጎዱ ሰዎችን እንደ ጉዳታቸው ዓይነት ድጋፍ ማድረግና መርዳት።

**መምህር:** አልማዝ ለሰጠችው መልስ በምሳሌ ግልጽ ሊያደርግ የሚችል ካለ?

**ሙፍሪያ:** በጦርነት ምክንያት የተለያዩ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል፣

**ወንድወሰን:** በተለያዩ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት መጠለያ ላጡ ሰዎች መጠለያና

ምግብ እንዲገኙ ያደርጋል።

መምህር: በጣም ጥሩ ! ሌላስ?

ዑመር:ረሃብና ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የተራቡ ሰዎችን መመገብ።

መምህር:ቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ ከላይ የዘረዘራችኋቸውን ድጋፎች ለማድረግ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚያደርግለት ማነው

አብርሃ: በጎ አድራጊ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና መንግሥታት።

መምህር: በጣም ጎበዝ ! እነዚህ በጎ አድራጊ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና መንግሥታት እንዴት ነው ድጋፍ የሚያደርጉት

ኦኮክ: የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ሲከሰቱ በአካል በመገኘት በግላቸው ድጋፍ ማድረግ፣ ሰዎች ድጋፍ እንዲያደርጉ በማስተባበር፣ ድርጅቶች ለዚህ ተግባር የተመደበ በጀት ካላቸው በመለገስ ወዘተ

መምህር: ኦኮክ የሠጠውን መልስ በምሳሌ የሚያስረዳ ካለ

ቢራራ: በ1977 ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ረሃብ ተከስቶ ማይክል ጃክሰንን ጨምሮ ታዋቂ የዓለም አርቲስቶች የሚዚቃኮንሰርት በማዘጋጀት ከፍተኛ ገቢ አሰባስበው በረሃብ የተጎዱ ወገኖችን ረድተዋል።

ዮሚፍ: ጃፓን በተደጋጋሚ በተከሰትባት የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የዓለም ሀገራት ድጋፍ አድርገውላታል።

መምህር: ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና መንግሥታት በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ድጋፍ ለማድረግ የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው

መሠረት:ሰብዓዊነታቸው። መልካም ሰብዓዊነት ካለ ሁሉም ከመረዳዳት ወደ ኋላ አይልም።

መምህር: በውይይታችን መሠረት ቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ ማለት በሰዎች በጎ ፍቃድ የተመሠረተ፣ በግለሰቦች፣ በድርጅቶችና በመንግሥታት የሚደገፍ በጎ አድራጊ ድርጅት ነው ብለን ልንገልጸው እንችላለን።

መምህር: ሁላችሁም ጥሩ ተሳትፎ አድርጋችኋል። በውይይቱ ስለ ቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ ግንዛቤ አግኝታችኋል። እኛም በሰብዓዊነት መረዳዳት እንዳለብን ተምረናል። ለዛሬ ውይይታችንን በዚህ እንቋጫለን።



## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በላይ የቀረበውን ውይይት መሠረት በማድረግ፣ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶች በኢምቁ ለመምህራችሁ ግለጹ።

1. ቀይ መስቀል/ ቀይ ጨረቃ እንዴት ሊገለጽ ይችላል?
2. ቀይ መስቀል የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ምን-ምን ናቸው?
3. ቀይ መስቀል ቀይ ጨረቃ ድጋፍ የሚያደርግበትን የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚያደርግለት ማነው?
4. በውይይቱ ውስጥ የተጠቀሱ ድጋፍ የተደረገላቸው ሁለት ሀገራት ማንና ማን ናቸው?
5. ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና መንግሥታት ለቀይ መስቀል ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው?

## ክፍለ ትምህርት አራት

የተለያየ ይዘት ኖሯቸው በተመሳሳይ ምልክት የሚገለጹ ምልክቶችን መተንተን።

*ቀይ መስቀል፣* የሚለው ምልከት በተለያዩ አገባቦችያሉትየተለያዩምልክቶች፣

1. አንተነህ በአንገቱ ቀይ መስቀል አስሯል።
2. የሥጋ ቤቱ በር ላይ ትልቅ መስቀል በቀይ ቀለም ተስሏል።
3. ቀይ መስቀል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ድጋፍ ያደርጋል።

*ቀይ ጨረቃ፣* የሚለው ምልክት በተለያዩ አገባቦች ያሉት የተለያዩ ምልክቶች፣

1. ዛሬ ምሽት የወጣችው ጨረቃ ቀይ ናት።
2. ቀይ ጨረቃ የተለያዩ ድጋፎችን የተለያየ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ያደርጋል
3. በአብዛኞቹ የሙስሊም *ሥጋ* ቤቶች በር ላይ የቀይ ጨረቃ ምልክት ይደረጋል።

## መልመጃ ሦስት

ከላይ የቀረበውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ፣ ለሚከተሉት ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላት ያላቸውን የተለያዩ ምልክቶች ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. *ኦክስጂን*

   ጓደኛዬ በጣም ስለታመመ ሐኪሙ *ኦክስጂን* እንዲደረግለት አዘዘ።

   ወደሰውነታችን የምናስገባው አየር *ኦክስጂን* ይባላል።

2. *መርፌ*

   አልማዝ የተቀደደ ቀሚሷን *በመርፌ* ጠቀመች።

   አበበች ጉንፋን ስለያዛት ሁለት *መርፌ* ተወጋች

3. *አልኮል*

   *አልኮል* አብዝቶ መጠጣት ለጤና ጠንቅ እንደሆነ ሐኪሞች ይናገራሉ

   ቁስል ላይ *አልኮል* ማድረግ ቁስሉ ቶሎ እንዲደርቅ ያደርጋል።

4. *ጥጥ*

   እናቴ ሁልጊዜ *ጥጥ* ትፈትላለች።

   ነርሷ የበሽተኛውን ቁስል *በጥጥ* ጠረገችለት።

5. *መቀስ*

   አትክልተኛው የተከለውን ጥድ *በመቀስ* ከርክሞ አስተካከለው።

   *መቀስ*፣ ዳቦ ቆሎ ለመቁረጥ፣ ጨርቅ ለመቁረጥ፣ ጸጉር ለማስተካከል ይጠቅማል።

## መልመጃ አራት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ምልክቶችን ለሚወክሉ ቃላትና ሐረጋት ትክክለኛ የኢምቋ አጠቃቀማቸውን ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. ኪኒን
2. መድኃኒት
3. ሐኪም ቤት/ሆስፒታል
4. ፋርማሲ
5. ፋርማሲስት
6. ቀዶ ጥገና (ለተለያዩ ቦታዎች የሚደረጉ ቀዶ ጥገናዎች የተለያዩ ምልክቶችን አሳዩ)
7. ነርስ
8. ሐኪም
9. ጤና ጣቢያ
10. ሽሮፕ

## ክፍለ ትምህርት አምስት

### የመስክ ሥራ

ከጋዜጣ፣ ከኢንተርኔት፣ ከመጽሔት፣ ወዘተ፣ የቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ አመሠራረት፣ የተመሠረተበት ዓመት፣ ሀገር፣ በአሁኑ ወቅት ዋና ጽ/ቤቱ የት ሀገር እንደሚገኝ አፈላልጋችሁ በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ።